# <u>መልስ ለበዕውቀቱ ዘኢትዮጵያ</u>

<u>ጌታቸው ረዳ ኢትዮጵያን ሰማይ አዘጋጅ</u>



ኢትዮጵያ ሐገሬ ስንቱን ደንቆሮ ነው ተሸክመሽ ያማጥሺው? መጥኔ ይስጥሽ ይላሉ የአማራ ሊቃውንቶች። ውጭ አገር ያለው ደንቆሮማ በሰለጠ አገር እየኖረ ከመሰልጠን ይልቅ ድሮ ታሽጎ እንነበረባት ዓለም ውስጥ እራሱን አስገብቶ መልሶ ሲደነቁር ስመለከት ከዚህ ስልጡን ዓለም ሌላ ወዴት ቢሄድ እንደሚሰለጥን ለኔ መልሱ የማላገኝለት ጥያቄ ነው።  አቶ በዕውቀቱ ዘኢትዮጵያ ጽሑፉክን ያገኘሁት በወልቃይት.ካም ውስጥ የተለጠፈ ሲሆን ምንጩ እዛው ወልቃይት ይሁን አይሁን አላወቅኩም። መጀመሪያ ነገር ለእንዲህ ያለ ጸሑፍ መልስ ለመስጠት ከልጆች ጋር የመነታረክ ያህል ስለምቆጥረው መልስ ልጽፍ አልፈለግኩም ነበር፡ ሆኖም ዘረኛነትን የተሞረኮዘ ጽሑፍ ስለሆነ ፖለቲካውን እያስታከኩ ትግሬነቴን ለመጐነታታል የሚቃጣቸው እንደ “በዕውቀቱ ዘኢትዮጵያ” ፤ እና እንዲሁም እንደ “የኢሕአፓ ካልቶች” የመሳሰሉ በድርጅትም ሆነ በግለሰብ የሚጽፉ ጎሰኞችን ባይበዛም መልስ መስጠት ስላለብኝ ‘ለምን ናቅከኝ እንዳይል መልሴም ይኼው ባጭሩ።

በመጀመሪያ አንባቢዎቼን ለማስገንዘብ የምፈልገው፤ ስማቸውን የሚደብቁ፤ ፎቶግራፋቸውን ለሕዝብ የማያሳዩ፤ ማንነታቸውን ላለመግለጽ የሚፈሩ ፈሪዎች ጋር መልስ መሰጣጣት ፈሪና ጎበዝ አብሮ እንደማይሄድ እንድታውቁልኝ ሁሌም የማስገነዝባችሁ ጉዳይ ነው። ይህ ሰውም ሆነ በርካታ ጸሐፊዎች ለምን ትክክለኛ ስማቸው ከነ ፎቶግራፋቸው ከአንባቢዎቻቸው ጋር ለመተዋወቅ እንደሚፈሩ ብትጠይቁ፤ አንድ የምትረዱት ነገር “የሚፈሩት ነገር ስላለ ድፍት ያጣሉ”። ድፍረት የሚያጡ ደግሞ እንደ ዓይጥ ተሸሽጎ መጮሕ ለፍርሃታቸው እንደድፍርት የሚተኩበት ዘዴ ነው። እራሱን ለአደባባይ ማሳያት ያልፈቀደ ደግሞ ‘ታማኝ’ አይደለም። ከትግሉም መራቅ አለበት። ተንኮለኛ ነው፤ ፈሪ ነው ማለት ነው። እንዲህ ያሉ ዜጎች ደግሞ መጥፎ ነገር ከመስራት አይቆጠቡም። ከራሳቸው ጋር ግንኙነት የላቸውም፤ ከራሳቸው ጋር አምነትና ውል አላደረጉም።ባጭሩ ከራሳቸው ጋር ያልተማማኑ በውጭ አምነት ሊያሳድሩ ከቶ ባሕሪያቸው አይፈቅድላቸውም። ስለዚህ እባካችሁ በይፋ ማንነታችሁን ማሳየትን ተለማመዱ፡ የሚያስፈራ ዓለም አድርጋችሁ አትዩ። ፍርሃትን ከሰበራችሁ ማንነታችሁ ኩራትን ያጎናጽፋል እና ከፍርሃት ቆፈን ሰብራችሁ ውጡ። ወንጀል የሰራችሁ የድሮ <u><ባለጌ ፖለቲከኞች></u> ካላችሁም ፖለቲካው ውስጥ አትግቡ። በድብቅ በሌላ ስም መዋሸት ይቻላል ፤ መድረኩ ግን ለናንተ አይመችም ።

በሃሰት ስም የሚጽፉ ሰዎቸ እውነት እላቸኋለሁ ብዙዎቹ ስለምንቃቸው መልስ አልሰጣቸውም። እራሱን ከሚሸሽግ ፈሪ ለምን ተብሎ ንትርክ? ለዚህ ፈሪ ግም መልስ መጻፍ ይቻላል ግን ከግም ጋር መነታረክ ትምሕርት አያፈራም። ልመልስለት የፈለግኩበት ምክንያት፤ ይህ ሰው ጽሑፉን ሲጀምር "በዘረኝነት" ስለሆነ። ድረገጾች ስማቸውን የሚደብቁና ዘረኛነትን የሚያስፋፋዩ ሁሉ ማስተናገድ አልነበረባቸውም፡ ሆኖም ለዛሬ ተቀብየዋለሁ። በዕውቀቱ ዘኢትዮጵያ ጽሁፉ ሲጅምር "የእባብ ልጅ እባብ እንደሚባለው ሁሉ ይህ ግለሰብ'' ብሎ ነበር የጀመረው። ብዙ ዘረኞች በየሚዲያው ተባዝተው ብዙ ጥፋት እያስከተሉ መሆናቸው ደጋግሜ ገልጫለሁ፡ በግልጽም ታግያቸዋለሁ። አባ መላ የተባለ ሰው ካሁን በፊት ትግሬዎች እባቦች የእባብ ልጅ እባብ ናቸው" ሲል በግልጽ መናገሩ ይታወቃል። ይህ በዕውቀቱ ዘኢትዮጵያ በሚል የውሸት ስም የመጣው ሰውየ ደግሞ፤ እኔን ብቻ ሳይሆን የማያውቃቸውን የኔን ወላጆችና የኔ ዘሮች የሆኑትን ትግሬዎችን ነው እባብ እና የእብብ ልጅ እያለን ያለው። ስማቸውን ለመደበቅ የሚገደዱ እንደዚህ ዓይነቶቹ 'በሽተኞች' አንዱ ምክንያታቸው ደግሞ ዘረኝነታቸው እንዳይታወቅባቸው ነው ተደብቀው በውሸት ስም እየመጡ ያችን የተጠናወታቸውን በሽታ ሲወረውሩ የምናየው። ችግራቸው ግን ፤እየታገሉት ያለው ሰውየ በቀላሉ የሚፈታ እየመሰላቸው ይመስለኛል፤ ሲንዘላዘሉ "እስቅባቸዋለሁ"።

በዕውቀቱ ዘኢትዮጵያ እባክህን እውነት እኔን ለመከራከር 'ፍላጎት' ሲኖርህ መጀመሪያ ልትላቸው የፈለግካቸውን ነጥቦች አሳምረህ እወቅ። ጽሑፍህን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ያለውን አንብቤ ምንም ፍሬ ነገር ስላጣሁበት መልስ ልስጥ አልችልም። እኔ የጻፍኩዋቸውን እየለቀምክ ነጥብ በነጥብ ማሳየት ወይንም ማፍረስ ችሎታ ስላነሰህ በደፈና ወያኔ ነው፤ የእባብ ልጅ እባባ፤ ጌታቸው ጸረ ኢትዮጵያ ነው........እንዲህ ያሉ ነገሮች ተይዞ አደባባይ አይወጣም (እንዲህ ያለ - ፓል ቶክ ውስጥ ውሰደው)። እኔ የተቃወምኳቸው ግለሰቦች፤ ድርጅቶች፤ መሪዎች እኔ ስለነሱ ያልኩትን "በመጥቀስ" እነዚያን በነጥብ በማፍረስ ለአንባቢዎችህ ማሳየት ነበረብህ፤ ግን አዝናለሁ አላደረግክም። ስለ ምታለቅስላቸው መሪዎችህም ሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች እና ግለሰቦች ብዙ ብያለሁ። እነሱን ለቅምህ መከራከር አለብህ። ካልሆነ ስለ እነሱ ያልኳቸውን ነጥቦች እንዳሉ ናቸው እና "እንዲሰሩ እየፈቀድክ ነው ማለት ነው"። የኔ ወንድም፤ ለሚዲያው አዲስ ከሆንክም 'ሰከን' በል እና ጊዜ ወስደህ ፖለቲካውን ማጥናት ነው። ካልሆነ እንደ ኢሕአፓዎች እና እንደ ግንቦት 7 ካልቶች የሚወቀሱበትን ነገር እየዘለሉ መልስ ሲያጡ በደፈናው እንደ አንተው እንደ የወንዝ ዳር የማታ ዕንቁራሪት ላንቃን ማስጮህ የሚወቀሱባቸውን ወቀሳዎች ሊቋቋሙ አይቻላቸውም።

አንተም ማድረግ የሚገባህ (ልመክርህ የምፈልገው) ጽሑፍህ ሳየው "ለፖለቲካው አዲስ ተለማማጅ" ትመስለኛለህ እና እኔ ስለምወቅሳቸው የፖለቲካ አለቆችህ ካሉ፤ ወይንም ግለሰቦች፤ ድርጅቶች ፤እኔ ስለ እነሱ አንስቼ የተናገርኳቸውን "በነጥብ" ማሳየት እና ከኔ ማብራርያ መሻት ይጠበቅብሃል። የምመክርህ ያ ነው። ስለዚህ ሰከን ብለህ ተማር። በፖለቲካው ብዙ ቆይቻለሁ፡ ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው፤ የሚባል አባባል አለ፤ ካንተ ይልቅ እኔ ለበርካታ አመታት ድርጅቶችን ፤ ፖለቲከኞችን፤ ከያኒየኖችን፤ ሃያሲያኖችን እና ጋዜጠኞችን ከነ ሚዲያዎቻቸው ስለማውቃቸው ...ያዲስ አበባ ልጆች እንደሚሉት ሰከን በል

፤ <<ተረጋጋ>>። ስለምታቆለጳፕሳቸው እና ሮማንትሳይዝ ከምታደርጋቸው እንደ ታቦት አይነኩብኝ የምትላቸው የፖለቲካ ጣኦቶችህ <<ከነበር አፍ ያመለጠው ፤ የኣዞ አፍ ተቀበለው>> እንዳትሆን አምላኪ መሆንህን አቁም።

“ካለመቃወም፤ካለመጻረር” የሚመጣ ዕድገት እና ክስተት የለም። ሰላምን ለማወቅ፤ ‘ጦርንተን፤ሃዘን” ካልኖረ፤ ፍቅርን ለማወቅ፤ጥላቻን ማወቅ፡ ሃዘን ፤ ፍቅር እና ክዳት ባይፈጠሩ “ሙዚቃ ባላስፈለገ” ባልተፈጠሩ ነበር።፡ እነዚህ ሁሉ ተቃራኒዎች ናቸው። ያለ ”ኮንትራዲክሽን” ራሳቸው ህይወጥ ሊኖራቸው አይቻላቸውም። ማንም ሳይነካቸው ዝም ብለው ፖለቲካውን ይምሩት፤ወደ ወያኔ ዓይናችሁ አትኩሩ የምትለው ጮርቃ ሕሊናሕ ከዓለም አፈጣጥር ሕግ አይሄድም። አለቆችህ ስቃወም፤ ያለ እኔ አይኖሩም፤ እኔ ስወቅሳቸው እና ሳጋልጣቸው አዋቂዎች ከሆኑ ያንን እርማት ይጠቀሙበታል፤ “ደነዞች” ከሆኑ ደግሞ እንዳንተው ያሉ በገፍ እያዶሎዙ ፤ እራሳቸውና ዶሎዞቻቸው በተቺዎች ብዕር እየተነረቱ ፤ መጨረሻ ላይ ጉብጠው ይኖራሉ። ስለዚህ መቃወም ከሌለ ምን ለማግኘት እንደምትሮጥ አታውቅም ማለት ነው።ካልታረምክ ትቆሽሻለህ። አንድ በጣም ችግር ሆኖ ያለው ነገር (በተለይ እዚህ ውጭ አገር)፤ ተቃዋሚዎችን አትንኩ፤አትውቀሱ ‘ወያኔ’ ብቻ አትኩሩ የሚል ባሕል የሚሰብኩ “ኢትዮጵያውያን” በፖለቲካው ያልሰለጡኑ ወይንም “ወንጀል” የሰሩ ሆኖው ተቺዎቹ እነሱም ጋር እንዳያነጣጥሩ እንደ “ማምለጫ” የሚጠቀሙበት ዘዴ ነው። እንዲህ አይነት ባሕል የሚከተል ማሕበረሰብ የሚደብቀው የፖለቲካ ባሕል አለ። እንዲህ ያለ እምነት የሚከተሉ ተቃዋሚ ደጋፊዎች የወያኔ መውደቅ ጉጉት ተሸንፎ መሰል ወንጀለኞቹንም ኪሱ ውስጥ ይዞ <<ከነበር አፍ ያመለጠው ፤ የኣዞ ኣፍ ተቀበለው>> ሲሳይ መሆናቸውን ጭራሽ አይታያቸውም።

ተቃዋሚው ክፍል በዚህ በሽታ ከተሰቃየ በርካታ አመታት ሆኖታል። በተቃዋሚው ውስጥ የተሰገሰጉ ተኩላዎች ፤ጅቦች ብዙ ሰው የገደሉ ወንጀለኞች፤ገራፊዎች እና አታላዮችን የማምለክ አባዜ ተይዞል። ወንጀለኞች፤ አታላዮችን፤ሓሰተኞችን ይወዳሉ። ለኔ በጣም ይገርመኛል። ይህ ባህሪ ከርሞ ጥኟ ነው። ስለሆነም ይታሰብበት። ወያኔ በሦስት ወር መውደቁ ነው እና የኛን አታላዮችና ነብሰገዳዮችን፤ሓሰተኞችን አትንኩ፤ እባቡንም ሰውኑም በጉም ጅቡም አብተን ይዘን ዝም ብለን እንገስግስ እና ሗላ ተሸክመን ያመጣናቸው ኣዞዎች ቢውጡንም ግድ የለም ከነብሩ ይልቅ አዞው ይዋጠን የሚሉ ተቃዋሚ ደጋፊዎች በጣም ተበራክተዋል። እባካችሁ ስሜታችሁን ተቆጣጠሩት እና ተረጋጉ። ነብርም ኣዞም አጥፊዎቻችሁ ናቸውና ከዚህ ድንቁርና ተሎ ውጡ!

አቶ በዕውቀቱ ዘኢትዮጵያ በዚህ የትግርኛ ምሳሌ ልደምድም ። <<ንምራኽስ እናኣ ሓቲትካ ተዋገያ>> ይላሉ አንተ እባቦች ብለህ የምትዘልፋቸው ቤተሰቦቼ ሲተርኩ። ትርጉም (ጥጃን ለመግዛት ስትፈልግ ጥጃዋን ሳይሆን ከእናትዋ ጋር ተገባይ) ይባላል። ለፖለቲካው ግብይት ስላልበሰልክ ፤ አለቆችህ እነማን መሆናቸው ካወቅህ እነሱን ላክ እና እራሳቸው ይከላከሉ።

ጌታቸው ረዳ getachre@aol.com